ቀልጣፋ የባንክ አገልግሎት በኢንተርኔት !

ባንካችን ወደ ቅርንጫፍ መሄድ ሳያስፈልግዎ ባሉበት ቦታ፣ በማንኛውም ሰዓት ምቾትዎ እንደተጠበቀ ቀልጣፋ የባንክ አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበትን የኢንተርኔት ባንኪንግ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ አድርጓል፡፡

የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት የባንክ ደንበኞችን እንቅስቃሴ መቆጣጠር፣ የባንክ ሂሳባቸውን መከታተል፣ ገንዘብ በቀላሉ በተቀላጠፈ መንገድ ማስተላለፍ የሚያስችል ዘመናዊ የባንክ አገልግሎቶችን የያዘ ነው፡፡

1. የኢንተርኔት ባንኪንግ ምንድን ነው?

ኢንተርኔት ባንኪንግ ማለት ደንበኛ ሳይንቀሳቀስ በባንኩ ድረ-ገጽ (Website) አማካኝነት በኢንተርኔት የሚሰጥ የባንክ አገልግሎት ነው፡፡ ይህ አገልግሎት በምንኛውም ደንበኞች ወደ ባንክ ቅርንጫፍ መሄድ ሳያስፈልጋቸው ከሥራ ቦታ፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ካለበት ቦታ ሆነው ወይም ከማንኛውም ሆነ በዓለም ዙሪያ ውጭ እንዲሁም ከሀገር ላይ እያሉ የሚያገኙት አገልግሎት ነው፡፡ አገልግሎቱ ባንኩ ራሱ በሚያስተዳድረው ድረ-ገጽ (Website) የሚሰጥ በመሆኑ የደንበኞች ሂሳብ እንቅስቃሴ ከደህንነት ስጋት የጸዳ ነው፡፡

1.1. የኢንተርኔት ባንኪንግ አስፈላጊነት

- በማንኛውም ሆነ በሥራ ቦታ የባንክ አገልግሎት ያገኛሉ፣
- ምቾትዎ እንደተጠበቀ ሆኖ ሳምንቱን በሙሉ በቀን 24 ሰዓት አገልግሎት ያገኛሉ፣
- የባንክ አገልግሎት ሲፈልጉ ወደ ባንክ ቅርንጫፍ መሄድም ሆነ ተራ መጠበቅ ሳያስፈልግዎ አገልግሎት ያገኛሉ፣
- የባንክ ባለሙያ ድጋፍ ሳያስፈልግዎ ራስዎ አገልግሎት ያገኛሉ፣
- እንደ ደንበኛው ፍላጎት እ.ኤ.አ. ከ2012 ጀምሮ በቀን ያሉዎትን የሂሳብ እንቅስቃሴ ባንክ ቅርንጫፍ መሄድ ሳያስፈልግዎ ማተም ወይም ማየት ይችላሉ፣
- ድርጅቶች የሠራተኞቻቸውን ደመወዝ መክፈል ያስችላቸዋል፣
- ድርጅቶች ደንበኞቻቸው ባሉበት የሥራ ቦታ ክፍያ እና የገቢ ሰነድ መቆጣጠር ያስችላቸዋል፣
- በአጭሩ ባንኩን ወደ ፈለጉበት ቦታ ይዘው ይሄዳሉ፡፡

1.2. የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

- ቀድሞ ሲል በባንኩ ሂሳብ ከሌለዎት በአቅራቢያዎ በሚገኝ ቅርንጫፍ የቁጠባ ወይም የተንቀሳቃሽ ሂሳብ ሊከፍቱ ይገባል፣
- ሂሳብዎ ወደ ሚገኝበት ቅርንጫፍ በመሄድ የማመልከቻ ቅጽ በአግባቡ መሙላት፣
- ቅጹን ከሞሉ በኋላ ከባንኩ የሚሰጥ የመጠቀሚያ የሚስጥር ስም (User ID)፣ የኪስ የደህንነት ቁልፍ (Pocket Token) እና የሞባይል የደህንነት ቁልፍ (Mobile soft token) ይሰጥዎታል፣
- የኢንተርኔትም ሆነ የኮምፒውተር አጠቃቀም መጠነኛ ዕውቀት፣
- የኢንተርኔት አገልግሎት የሚያገኙበት ኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት በአግባቡ የሚሰጥ ተንቀሳቃሽ ስልክ፡፡

1.3. የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት እነማን ናቸው?

ማንኛውም የባንኩ ደንበኛ የሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፡፡

1.4. በአንድ ጊዜ እስከ ስንት ብር ድረስ ገንዘብ ማስተላለፍ ወይም ማዘዋወር ይቻላል?

በኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት የገንዘብ ዝውውር መጠን እንደ ሁኔታው የሚቀየር ሆኖ በአንድ ቀን (በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ)፦

- የግል የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚ ደንበኞች እስከ ብር 100,000 ለሌሎችም ሆነ ቀድሞ ለተመዘገቡ ተከፋይ ማስተላለፍ ይችላሉ፤ እንዲሁም ደንበኛው ወደራሳቸው ሂሳብ/ሂሳቦቻቸው ያለምንም ገደብ ገንዘብ ማስተላለፍ ይችላሉ፣
- የድርጅት የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚ ደንበኞች ለሌሎችም ሆነ ቀድሞ ለተመዘገቡ ተከፋይ/እንዲሁም ደንበኛው ወደራሳቸው ሂሳብ ያለምንም ገደብ ገንዘብ ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

1.5. በምን ሰዓት ጊዜ ገንዘብ ማስተላለፍ ወይም ማዘዋወር ይቻላል?

በአንድ ቀን (በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ)

- የግል የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚ በተደጋጋሚ በባንኩ ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች ሰዎች ሂሳብ ወይም በሌሎች ተከፋይ ለሚሆን ግለሰብ ገንዘብ ማስተላለፍ ወይም ማዘዋወር የሚችለው በቀን የተፈቀደው የገንዘብ መጠን ብር 100,000 እስኪሞላ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም የግል የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚ በአንድ ደንበኛ ቁጥር ወደተመዘገቡ የራሱ ሂሳብ ገንዘብ የሚያስተላልፍ ወይም ሂሳብ የሚያዛውር ገደብ የለበትም፡፡
- የድርጅት የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚ በተደጋጋሚ በባንኩ ውስጥ ለሚገኝ ለሌላ ሰው ሂሳብ ወይም በሌላ ተከፋይ ለሚሆን ግለሰብ ገንዘብ ማስተላለፍ ወይም ማዘዋወር ገደብ የለበትም፡፡

1.6. በኢንተርኔት ባንኪንግ አማካኝነት ምን ምን አገልግሎቶችን ማግኘት ይቻላል?

የገንዘብ እንቅስቃሴን በተመለከተ

- ደንበኞች ለሚፈልጉት ተከፋይ በጊዜ ገደብ የተወሰነ የገንዘብ መጠን ከሂሳባቸው እየተቀነሰ እንዲተላለፍ ወይም ክፍያ እንዲፈጸም ቋሚ የክፍያ ትዕዛዝ መስጠት፣
- ደንበኞች በባንኩ ውስጥ ሂሳብ ላለው ደንበኛ ገንዘብ ማስተላለፍ ወይም ክፍያ መፈጸም እንዲሁም በባንኩ ሂሳብ ለሌለው ተከፋይ ሐዋላ መላክ፣
- በባንኩ ቅርንጫፎች ያሉዎትን በአንድ የደንበኛ መለያ ቁጥር (Customer ID) የሚገኙ ሂሳቦችዎን በቀላሉ ማንቀሳቀስ፣
- ከአንድ በላይ ሂሳብ በተለያዩ የባንኩ ቅርንጫፎች ካሉዎት ከአንዱ ሂሳብ ወደ ሌላኛው ሂሳብ ገንዘብ ማዘዋወር፣
- ድርጅቶች በአንድ ጊዜ የብዙ ሠራተኞችን ደመወዝም ሆነ ሌላ ክፍያዎችን መፈጸም

የሂሳብ መረጃን በተመለከተ

- ደንበኞች በባንክ ሂሳባቸው ያለውን ቀሪ ገንዘብ ማወቅ፣
- ደንበኞች በባንኩ ሂሳባቸው ላይ የተካሄዱትን ወይም የተደረጉትን ገቢዎች እና ወጪዎች ማወቅ፣
- እ.ኤ.አ. ከ2012 ጀምሮ በቀን በሂሳብዎ የተካሄዱ የወጪና የገቢ ዝርዝር መግለጫዎች ማየት ወይም ማተም፣
- ደንበኞች ወደ ባንኩ መልዕክት መላክ እንዲሁም ከባንኩ የሚላኩ መልዕክቶችን መቀበል፣
- ደንበኞች ቼክ የክፍያ ትዕዛዞች እንዲተላለፉላቸው የሚያስገቡትን ማሳሰቢያዎች መስጠት
- የተንቀሳቃሽ ሂሳብ ያላቸው ደንበኞች የቼክ ደብተር እንዲታተምላቸው መጠየቅ/ማዘዝ
- የተንቀሳቃሽ ሂሳብ ያላቸው ደንበኞች በቼክ የከፈሏቸውን ክፍያዎችን መከታተል
- የተንቀሳቃሽ ሂሳብ ያላቸው ደንበኞች የሰጡት ቼክ ክፍያ ስለመፈጸሙ ሁኔታ መከታተል የሚከናወኑትን አገልግሎቶች ማግኘት
- የውጭ ምንዛሬ የክፍያ ፕሮግራሞችን ማወቅ
- የዕለቱን የምንዛሬ ዋጋ ማወቅ
- የብድር ክፍያ ፕሮግራሞችን፣ ቀሪ ተቀማጭ ሂሳብ፣ወለድ፣ቀሪ ዕዳ ማወቅ
- የሚጠቀሙበትን የሚስጥር ቁጥር መቀየር መቻል
- የኪስ የደህንነት ቁልፍ የሚስጢር ቁጥር ሲጠፋ ተጠቃሚው መቀየር

1.7. በኢንተርኔት ባንኪንግ ለመጠቀም የአገልግሎት ክፍያ አለው?

ባንኩ በአሁኑ ጊዜ የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚ ደንበኞች በባንኩ ውስጥ ለሚገኙ ወደሌላም ሆነ ወደራሳቸው ሂሳብ ገንዘብ ለማስተላለፍ ወይም ለማዘዋወር ምንም ዓይነት የአገልግሎት ክፍያ አያስከፍልም፡፡ ሆኖም በኢንተርኔት ባንኪንግ ለሚፈጸም የሐዋላ አገልግሎት በባንኩ ቅርንጫፎች የሚጠየቀው ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ወደፊት እንደሁኔታው እንደ አስፈላጊነቱ ለተለያዩ የአገልግሎት ክፍያዎች እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡

1.8. የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት የሚያገለግለው ለምን ያህል ጊዜ ነው?

አንዴ የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ከተመዘገቡ በኋላ የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ብቻ ነው፡፡ ሆኖም በአያያዝ ጉድለት የተነሳ የደህንነት ቁልፉ ቢበላሽ ወይም የሚስጢር ቁጥሩን ቢረሱት በምትኩ አዲስ የደህንነት ቁልፍ በክፍያ ያገኛሉ፡፡ የአገልግሎቱ ጊዜው ሲያበቃም አገልግሎቱን ወደአገኙበት ቅርንጫፍ በመሄድ ማደስ ይቻላል፡፡

1.9. የባንኩ የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ምን አድርጓል?

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የደህንነት መስፈርቶችን አሟልቷል፡፡ እነዚህም፦

- በአካልም ሆነ በሲስተም የተጠናከረ መጠበቂያ (Firewalls) ያለው የመረጃ ማዕከል
- አስተማማኝ ባለው ዓለም አቀፍ የደህንነት አካል ዕውቅና ያለው ድረ ገጽ
- አገልግሎቱን ለመጠቀም ከአንድ በላይ የደንበኛ ማረጋገጫ መጠቀም
- ድረ ገጹ ከተከፈተ በኋላ ያለ እንቅስቃሴ የሚቆይበትን ጊዜ መገደብ
- ድረ ገጹ ከተከፈተ በኋላ ለሚፈጸሙ እንቅስቃሴዎች ማረጋገጫ መጠየቅ

ተጨማሪም ጊዜውን የጠበቀ የኢንተርኔት ባንኪንግ ደህንነት ቴክኖሎጂ ተግባራዊ ለማድረግ ይተጋል፡፡

1.10. ደንበኞች ሊያደርጉት የሚገባ ጥንቃቄ ምንድን ነው?

ደንበኞች በባንኩ ከሚጠበቀው እና ከሌሎች ደረጃውን የጠበቀ የደህንነት ጥንቃቄ በተጨማሪ የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡፡

- የሚጠቀሙበት ኮምፒውተር ሁሌም የቫይረስ መከላከያ እንዳለው ማረጋገጥ፣
- ደንበኛው ባለው እንቅስቃሴ ዝርዝር ሲጨርሱ ሲስተሙን መውጣትዎን ማስታወስ፣
- ሁልጊዜ ድረ ገጹ ሲገለገሉ ሲስተሙ የሚሰጠዎትን ምክሮች በሚገባ በጥንቃቄ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ባንኩ ከደንበኞች ጋር በኢሜይል ስለማይገናኝ በኢሜይል የሚደርሱ መልዕክቶችን አለማስተናገድ፣
- የኢንተርኔት ባንክ አገልግሎቱን ከተጠቀሙ በኋላ አስፈላጊውን ቅደም ተከተል በመከተል መውጣት/መውጫ (logout)፣
- የሚስጢር ቁጥርን /PIN/ በሚስጥር መያዝ፣
- የሚስጢር የደህንነት ቁልፍ (Pocket Token) ሲጠፋብዎ ደንበኛ ወደሚገኙበት ቅርንጫፍ በመሄድ ወዲያውኑ ማሳወቅ፣

1.11. የሚስጢር ቁጥር ቢረሱ ምን ማድረግ አለብዎ?

የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት ለመጠቀም የሚያስፈልጉትን የሚስጢር ቁጥር (Password) ቢረሱት አገልግሎቱን ማግኘት ስለማይችሉ ሊያስታውሱት በሚችሉት በመቀየር በሚገባ ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ምናልባት ያሉ ሚስጢር ቁጥሩን ቢረሱት አዲስ የሚስጢር ቁጥር ለማግኘት፦

- በመጀመሪያ የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት ተጠቃሚ ወደ ሆኑበት የባንኩ ቅርንጫፍ በመሄድ የክፍያ ቅጽ መሙላት ማቅረብ፣
- ባንኩ ያስመዘገቡትን የሚስጢር ቁጥር መቀየሩን ቀድሞ ማረጋገጥ፣
- ባንኩም በምትኩ አዲስ የሚስጢር ቁጥር ይሰጥዎታል፡፡

1.12. የሚስጢር የደህንነት ቁልፍ (Pocket Token) ቢጠፋ / ቢበላሽ ምን ማድረግ አለብዎ?

የሚስጢር የደህንነት ቁልፍ (Pocket Token) ቢጠፋ ወይም ቢበላሽብዎ ወዲያውኑ በባንኩ ቁጥር 8651 ያስመዝግቡ፡፡ ቀጥለውም የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት ተጠቃሚ ወደ ሆኑበት የባንኩ ቅርንጫፍ በአካል በመቅረብ ባንኩ የሚጠይቀውን ቅጽ በመሙላት መመዝገብዎን ተግባራዊ ያድርጉ፡፡ ባንኩም በምትኩ የሚስጢር የደህንነት ቁልፍ (Pocket Token) በክፍያ ይሰጥዎታል፡፡

1.13. የምስጢር ቁጥሩ በአጋጣሚ በሌላ ሰው ቢታወቅ ምን ማድረግ አለብዎ?

የምስጢር ቁጥርዎን ሰዎች ቢያውቁብዎ በኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት በመጠቀም የቀድሞውን ቁጥር የራስዎ በሆነ አዲስ የምስጢር ቁጥር መቀየር ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ የሚስጢር የደህንነት ቁልፍ (Pocket Token) የምስጢር ቁጥርዎን ሰዎች ቢያውቁብዎ የደህንነት ቁልፉን በመጠቀም የምስጢር ቁጥር መቀየር ይችላሉ፡፡

ማስታወሻ

የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎትን በተመለከተ ተጨማሪ መግለጫ እና የተለያዩ መመሪያ ሰነዶችን ለማግኘት ድረ ገጽ http://www.combanketh.et/EPayment/Internet Banking.aspx ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡

ፖ.ሣ.ቁ. 255
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ስልክ +251 11 551 50 04
+251 11 466 92 73
+251-11-466-97 38
ፋክስ 251 -11- 466-90-07
ኢሜል cbecsmu@combanketh.et
ድረ ገጽ www.combanketh.et
ስዊፍት ኮድ CBETETAA

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

ሁሌም የሚተማመኑበት ባንክ

በአዲሱ ኢንተርኔት ባንኪንግ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ባሉበት ቦታ ተጠቃሚ ይሁኑ!

እሴቶች
ተቀማጭ ሂሳቦች
የደንበኞች አገልግሎት
የአገልግሎት ዋጋ
መረጃዎች

በአዲሱ ኢንተርኔት ባንኪንግ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ባሉበት ቦታ ተጠቃሚ ይሁኑ!

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopian